## የማህበሩ መግለጫ

የያንዳንዱ ኣክሲዮን ዋጋ ብር 5,000 እና የኣክስዩን ስርጭት ወጪ 1% በኣክስዩን እንዲከፈል ሆኖ 6,000 የሚሆኑ የሰላም የህዝብ ማመላለሻ አ/ማ ኣክሲዮኖቹን በኣንድ ጊዜ ክፍያ ለመሸጥ የተዘጋጀ፡፡

6,000 ኣክሲዩኖች የያንዳንዱ ዋጋ 5,000 ብር የሆነ የሰላም ህዝብ ማመላለሻ አክስዮን ማህበር ለግለሰቦችና ለድርጅቶች፣ በመላው ኢትዩጱያ ውስጥ በሚገኘው የወጋገን ባንክ ቅርንጫፎች በኩል እንደሚሸጥ ሲገልፅ ደስታ ይሰመዋል፡፡ የኣክሰዩን ሽያጭ ምዝገባ የሚጀመርበት ቀን እ.ኤ.አ ጥቅምት 02 2006 ሲሆን ታሕሳስ 31 2006 ያበቃል፡፡

## ሰላም የህዝብ ማመላለሻ አክስዮን ማህበር

የምዝገባ ቁጥር መቀ/ንማ - 1.አ.0014/87

በትግራይ ክልል መቀሌ ንግድ ቢሮ

ጥር 29 ቀን 1987 የተመዘገበ

## ዋና መሥሪያ ቤት፣

ወረዳ 1 ቀበሌ 07 የቤት ቁ 469

የስልክ ቁጥር 0344 40 89 16

የፋክስ ቁጥር 0344 41 08 68

ፖስታ ሳጥን ቁጥር 60

መቀሌ፣ ትግራይ፣ ኢትዮጱያ

# 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ የመሬት ስፋት 1.1 ሚልዮን ስኬር ኪሎ ሜትር ሆኖ የህዝቡ ብዛት ደግሞ 77 ሚልዮን ሲሆን የመንገድ ዝርጋታውና ደረጃው ከአፍሪካ አገሮች ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛው ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡

በሃገራችን ከቦታ ወደ ቦታ ለመጓጓዝ 80% የሚሆነው ህዝብ የሚጠቀመው ተለምዶአዊ የሆነ ትራንስፖርት ማለትም በእግር መሄድ፣ በጭንቅላትና በጀርባ ተሸክሞ መሄድ እና በጀርባ የሚሸከሙ እንስሳት በመጠቀም ነው፡፡ በዚህ በጣም ኃላቀር የትራንስፖርት አጠቃቀም ምክንያት በገጠር የሚኖረው ህዝብ የጊዜና የጉልበቱ ብክነት አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል፡፡ የገጠር ህዝብ 85% በእርሻ የሚተዳደርበት አገር በዝርጋታውና በደረጃው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መንገድ ለምርታማነትና ባጠቃላይ ደግሞ ለአገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንቅፋት በመሆን ላይ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት በአሁኑ ወቅት የችግሩን አሳሳቢነት ተገንዝቦ የመንገድ ዝርጋታና ደረጃ መሻሻል ለሃገር ዕድገት እንደ ቅድመ ሁኔታ ወስዶ የአስር ዓመት የመንገድ ዘርፍ የዕድገት ፕሮግራም በ 19.3 ቢልዮን ብር በጀት መድቦ ፕሮጀክቱ ለማገባደድ በጥረት ላይ የሚገኝ ሲሆን ዋና ዓላማው ደግሞ የትራንስፖርት አገልግሎት ውጤታማና ወጪውን ቀንሶ የኦፕሬሽን ስራውን በማከናወን ምርታማነት፣ የምርት ስርጭትና ኤክስፖርትን በማቀላጠፍ የሃገር ኢኮኖሚን መገንባት ነው፡፡

77 ሚልዮን የህዝብ ብዛት ላላት አገር በጠቅላላ ያሉት የከፍተኛ አውቶብሶች ብዛት 1,000 አካባቢ በመሆኑ አንድ የከፍተኛ አውቶብስ ወንበር ለ1,283 ህዝብ በላይ ሊደርስ ችሏል፡፡ ከተጠቀሱት አውቶብሶች ውስጥ ደግሞ 90% የሚሆኑት በጣም ያረጁ ከመሆናቸው የተነሳ በአሁኑ ወቅት ለረጅም ጉዞ አስተማማኝና ምቾቱ የተጠበቀ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ናቸው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ዝርዝር ሁኔታዎች የሃገሪቱን ዕድገት ቀይዶ የያዘውን የመንገድ ትራንስፖርት ኣገልግሎት ለማሻሻል ከመነጨ ቀጥተኛ ቀና ኣስተሳሰብ ነው ሰላም የህዝብ ማመላለሻ አ/ማ ማቋቋም ያስፈለገው።

ፈጣንና አስተማማኝ የህዝብ ማመላለሻ አስተዳደር ለገጠርና ከተማ ትስስርና ኢኮኖሚያዊ ልማት ወሳኝ አስተዋፅኦ የሚደርግ ሲሆን የስራ ዕድል በመፍጠርና ለመኖርያ ቤት፣ ለስራ ቦታ እንዲሁም ወደ ትምህርት ቤት በቀላሉ ለማገናኘት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## 2. የሰላም ህዝብ ማመላለሻ አ/ማ አመሰራረት

መንግስት በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ የሆነ መዋዕለ ንዋይ መድቦ bሃገር ደረጃ የሚካሄደው የመንገድ ማሻሻልና በአስፋልት ደረጃ ማልበስ ስራ ጎን ለጎን ምቾቱ የጠበቀ በብቃትና በአስተማማኝ ሁኔታ አገልግሎት የሚሰጥ

የህዝብ ማመላለሻ ኩባንያ ማቋቋም ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ የሚከተሉትን ጥቅሞች እንደሚሰጥ ታምኖበታል

- ከሃገራችን የሚወጡትንና የሚገቡትን የሰዎችና የዕቃዎችን እንቅስቃሴ ማሻሻል፣
- የህዝብ ማመላለሻ ዋጋ የማረጋጋት ሚና መጫወት
- በክልሎች መካከል ጠንካራ የህዝብ ማመላለሻ ኔትዎርክ በመዘርጋት በህዝቦች መካከል ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ማጠናከር፡፡
- የኢኮኖሚ ዕድገትን በሃገሪቱ ቆዳ ስፋት በተስተካከለ መልክ ማፋጠንና ማሰራጨት፣
- በንግድ ዘርፍ በኩል ውድድርን ለማስፋፋትና በገጠርና በከተማ የሚገኘውን የኢንዱስትሪና የግብርና ዕቃዎች ስርጭት ዋጋ ማመጣጠን፣
- ለገጠሩ ሕዝብ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ገበያዎችን ክፍት ማድረግና እንዲገለገልባቸው ማገዝ
- የስራ እድል መፍጠር ናቸው::

### 2.1 ገበያን በተመለከተ

በህዝብ ማመላለሻ ሴክተር የተካሄደው የገበያ ጥናት እንድሚያመለክተው በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ከፍተኛ የሆነ የፍላጎት መጠን መጨመር እንዳለ ተረጋግጦል፡፡

ኩባንያው በአሁኑ ወቅት በፌደራል ደረጃ ተመዝግቦ የስምሪት መነሻው ከአዲስ አበባ ሆኖ ወደ ተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎቾ ማለትም መተማ፣ ሑመራ፣ እንዳስላሴ፣ አሶሳ፣ ጋምቤላ፣ መቱ፣ አርባምንጭ፣ ፣ ሞያሌ፣ ጅጅጋ፣ ድሬዳዋ ባሉት የትራንስፖርት መስመሮች ላይ እንደሚሰማራና የቱሪስት አይነት አውቶብሶቹ ደግሞ አስፋልት መንገድ ብቻ ያላቸው መስመሮች ማለትም ባህርዳር፣ ጎንደር፣ መቐለ፣ ድሬዳዋ፣ ሃረር፣ አዋሳ፣ ደሴ የመሳሰሉት መስመሮች አገልግሎት ለመስጠት በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

## 3. የገቢ ይዞታ

ኩባንያው ከተቋቋመ ከአስር ዓመት በኃላ የተካሄደው ጥናት እንደሚያመለክተው የሚከተሉትን የገቢ መመዘኛዎች ታሳቢ በማድረግ

- የኩባንያው ጠቅላላ አውቶብሶች 14 ባለ 60 መቀመጫና 20 ባለ 47 መቀመጫ የቱሪስት አይነት ኣውቶቡሶች ሆነው ፍሪጅ፣ ሞኒተር፣ አየር ኮንድሽነርና የመቀመጫ ቀበቶ ለያንዳንዱ ሰው ስላላቸው ተሳፋሪው በጉዞ ላይ በዲቪዲ/ቪሲዲ ፊልምና

ሙዚቃ እንዲሁም በድፎ ዳቦ፣ ቆሎ፣ ለስላሳ መጠጥና የታሸገ ፕላስቲክ ውሃ እየተዝናና የሚጓዝባቸው ዓይነት አውቶብሶች ናቸው፡፡

- ኣማካይ የጉዞ ርቀት በቀን በአንድ አውቶብስ 345 ኪ.ሜ ለ60 ሰው መቀመጫ ያላቸውና 390 ኪሜ ለ47 መቀመጫ ያላቸው አውቶቡሶች እንደሚሆን፣
- አንድ አውቶብስ በወር 24 ቀን እንደሚሰራ
- የተጓዥ ታሪፍ በሰው በኪሎሜትር 0.138 ብር በጠጠር መንገድ ሲሆን በአስፋልት መንገድ ደግሞ 0.11245 ብር ነው፡፡ ለቱሪስት ዓይነት አውቶብስ ደግሞ በአስፋልት መንገድ 0.20434 ብር በሰው በኪሜ እንደሚሆን፣
- የነዳጅ አጠቃቀም 3 ኪ/ሜ በሊትር ሲሆን የነዳጅ ዋጋ ደግሞ 5.85 እንደሚሆን
- የአንድ ጎማ ዕድሜ በአማካይ 35000 ኪሎሜትር ይሆናል
- የመለዋወጫ ዕቃ ዋጋ 0.35 ብር በኪሎሜትር ይሆናል
- የዘይትና ቅባት ወጪ 8% የነዳጅ ወጪ ይሆናል፡፡
- አማካይ የጭነት መጠን 85% ይሆናል

በዚሁ መሰረት የማህበሩ የኣመት የተጣራ ገቢ

ለባለ 60 ወ (345 x 14 x 12 x 24 x 0.3 x 0.11245 x 60 x 0.85) +

(345 x 14 x 12 x 24 x 0.7 x 0.138 x 60 x 0.85) እና

ለባለ 47 ወ (390 x 20 x 12 x 25 x 0.20434 x 47 x 0.85)

= 2,393,263 + 6,853,097 + 19,102,316 = 28,348,676

የአንድ አውቶብስ ኦፐረሽናልና አስተዳደራዊ ወጪ በዓመት በድምሩ 743ጪ407 እና የዕርጅና ቅናሽ ስሌት በ5 ዓመት እንዲሆን ያደረገ እሳቤ ነው፡፡ የዕርጅና ቅናሹ መጠን ከፍተኛ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በዓመት የሚገኘው ትርፍ 4,092,812 ብር ይሆናል፡፡

## 4. ስራውን ለመጀመር ስለሚያስፈልገው ወጪ

የአውቶብስ ዋጋ ብር 48,107,694 ሲሆን ለነዳጅ ማደያውና ሌሎች ቋሚ ንብረቶች ዋጋ ደግሞ 7,161,061 በመሆኑ በአጠቃላይ የሚያስፈልገውን ወጪ 55,268,755 ብር ሙሉ በሙሉ በትግራይ ልማት ማህበርና በባንክ ብድር የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## 5. የፋይናንስ ግምገማ

የዕርጅና ቅናሽ ጊዜ 5 ዓመት እንዲሁም የፕሮ•ክቱ ህይወት ከ10 እስከ 15 ዓመት እንደሚሆን ተገምቶ በ15% ቅናሽ የወለድ ዋጋ የተሰላው የድርጅቱ የፋይናንስ ግምገማ ፕሮጀክቱ ጤናማ የሆነ ውጤት እንዳለው አሳይቷል። ለዚህ የፋይናንስ ግምገማ ሚዛን የተወሰደው ገቢ አማካዩ በመሆኑ፣ የነዳጅ ማደያና የመኪኖች ጥገና አገልግሎት ስለሚሰጥ ከፍ ባለ የወለድ ዋጋ ተወስዶ የማህበሩ ፋይናንስ ቢመዘን ፕሮጀክቱ ጤናማ ውጤት እንደሚያሳይ ይታመናል፡፡

ማህበሩ በተከታታይ ኣመታት ተጨማሪ ኣውቶቡሶችን ቢገዛ የበለጠ አዋጪ እንደሚሆን ከግምገማው ለመረዳት ይቻላል፡፡

## 6. አደረጃጀትና ሎጂስቲክስ

- የጥገና ማዕከልና የመለዋወጫ ዕቃ በበቂ ሁኔታ ስቶክ መያዝ
- የሰለጠነ የሰው ሃይል መቅጠርና የፕላኒንግና የኦፕሬሽን የአሰራርና የቁጥጥር ዘዴዎች መዘርጋት
- የተከናወኑ ስራዎች መቆጣጠርና መገምገም

እነዚህ ስራዎች ለመፈፀም ዋና ስራ አስኪያጅ፣ ኦፕሬሽን መምርያ፣ የቴክኒክና አቅርቦት መምርያ፣ አስተዳደርና ፋይናንስ መምርያ፣ የኦዲት ግልጋሎት የፕላንና ማርኬቲንግ ግልጋሎትና የህግ ግልጋሎት መዋቅር ተዘርግቷል፡፡ ኩባንያው የሚተዳደረው በአምስት የቦርድ አባላት ነው፡፡ ዕለታዊ ስራ የሚመራና የሚቆጣጠር ዋና ስራ አስኪያጅና ማነጅመንት ይሰየማሉ፡፡

## 7. ድርጅቱ ኣሁን ያለበት አቋም

በኩባንያው ዕቅድ እንደተመለከተው፣ ሰላም የህዝብ ማመላለሻ አ/ማ ጥር 29 ቀን 1987 ዓ.ም ዋናው መ/ቤቱን በመቀሌ በማድረግ በንግድና ኢንዱስትሪ በንግድ ምዝገባ በቁጥር መቀ/ንግ-1.አ.0014/87 በተፈቀደለት መሰረት ተቋቁሟል።
ድርጅቱ በመነሻ ካፒታል ያስመዘገበውና የተከፈለው ካፒታል ብር 1,000,000 /አንድ ሚሊዮን/ ነው። በማቋቋሚያ ደንቡ ላይ እንደተቀመጠው ኩባንያው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የኩባንያ መስራች ኣባላት ኣሉት፣

| የኩባንያው ባለቤቶች | የአክስዮን ቁጥር | ዋጋ |
|---|---|---|
| 1. የትግራይ ልማት ማህበር | 996 | 996,000 |
| 2. ኣቶ ኣርኣያ ዘሪሁን | 1 | 1000 |
| 3. ኣቶ በቀለ ብርሃኔ | 1 | 1000 |
| 4. ኣቶ ገ/ሚካኤል ጳውሎስ | 1 | 1000 |
| 5. ኣቶ ታደሰ ተፈራ | 1 | 1000 |
| ጠቅላላ | 1,000 | 1,000,000 |

በአሁኑ ወቅት ኩባንያው 14 ባለ 60 መቀመጫና 5 ባለ 46 መቀመጫ ያላቸው የቱሪስት ዓይነት አውቶብሶች በመጠቀም ከአዲስ አበባ ወደ ተለያዩ የክልል ከተሞች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በቅርቡ ደግሞ በገበያ ከፍተኛ የሆነ ተቀባይነት ያገኙት 15 የቱሪስት ዓይነት አውቶቡሶች በማስመጣት ላይ ይገኛል፡ ኩባንያው ለ130 ሰዎች የስራ ዕድል ፈጥሯል፡፡

ባለፉት ሶስት አመታት የአውቶብሶቹ ጥራትና እድሜ ባለተጠበቀበት ሁኔታና መንገዱም እንደ አሁኑ ባልተጠገነበት ወቅትና አውቶቡሶቹ የሚሰማሩት ገበያን መሰረት አድርገው ሳይሆን ህዝብን ለማገልገል ተብሎ ከአቅማቸው በታችና አዋጭ ወደ አልሆኑት መስመሮች ጭምር እየተሰማሩ የተገኘው ትርፍ በውጭ ኦዲተሮች እንደተረጋገጠው ኩባንያው 197,033፣ 1,342,289፣ 769,813 ትርፍ በተከታታይ ለማስመዝገብ ችሏል፡፡

ኩባንያው ሲቋቋም የነበረው ካፒታል 13,762,626 ሲሆን ከዓስር ዓመት በኃላ በአሁኑ ወቅት ያለው ካፒታል ህንፃዎች ሳይጨምር በውጭ ኮንሰልታልቶች እንደተረጋገጠው 22,662,425 ሊደርስ ችሏል፡፡ ከዚህ ለመረዳት የሚቻለው የተጠቀሱት ችግሮች ተቋቅሞ በየአመቱ በአማካኝ 889,980 ብር የካፒታል ዕድገት ማሳየት መቻሉ ኩባንያው ገበያን ማእከል አድርጎ ሲሰማራ ምን ያህል ትርፋማ ሊሆን እንደሚችል በቀላሉ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አዲሶቹ አውቶቡሶች በአሁኑ ወቅት bÑlù አቅማቸው ኣገልግሎት በመስጠት ላይ በመሆናቸው በፕሮጀክቱ ጥናት እንደተመለከተው ኩባንያው በቂ ገበያ እንዳለውና አዋጪ የስራ ዘርፍ መሆኑ የሚጠቁም ሆኗል፡፡

## 8 የኣምስት ኣመት የፋይናንስ ዕቅድ

በሚቀጥሉት ኣምስት ኣመታት 1999-2003 ዓ.ም. ኩባንያው የሃብት ይዞታውን በሚያገኘው ትርፍና ከአክስዮን ሽያጭ የአውቶቡሶቹ ብዛት 75 አድርሶ ከብር 55 ሚሊዮን ወደ ብር 80 ሚሊዮን ማለትም በ46% ለማሳደግ ዕቅድ ኣለው፡፡ በተመሳሳይ ዓመታት ውስጥ የኩባንያው

ትርፍ በመጀመርያው ዓመት 4,092,812 ሲሆን በአምስት ዓመት ድምር ትርፍ ደግሞ 11.56 ሚልዮን ብር እንደሚደርስ ከተደረገው ጥናት ለመረዳት ይቻላል፡፡

**9 የሰላም ኣውቶቡስ ኣክስዮን ማህበር ለህዝብ ስለመሸጥ**

እየጨመረ የመጣውን የሕዝቡን የትራንስፖርት ፍላጎት ለሟሟላት እንዲሁም የማህበሩን የባለቤትነት ይዞታ ለመለወጥ፣ የማህበሩን መስራች ባለቤቶች በየካቲት 9 ቀን 1998 ዓ.ም በተካሄደው ጉባኤ የሚከተለውን ወስነዋል::

ሀ/ የትግራይ ልማት ማሕበር የባለቤትነት ድርሻ ለጊዜው 40% ሆኖ ቀስ በቀስ ደግሞ ያለውን ድርሻ ለህዝብ እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡

ለ/ ህዝቡ የማህበሩን ኣክሲዮኖች እንዲገዛና የማህበሩ ባለቤት እንዲሆን ዕድል መስጠት፣

ሐ/ የኩባንያው ንብረት ሕጋዊ በሆነ አማካሪ ድርጅት እንዲገመት የሚሉ ናቸው፡፡

**10. የትርፍ ክፍያ**

የትርፍ ክፍያ የሚከፋፈለው እያንዳንዱ ባለው የአክስዮን ብዛት የሚወሰን ሲሆን ጠቅላላ ጉባኤው ከተገኘው ትርፍ ምን ያህሉ ለባለአክስዮኑ መከፋፈል እንዳለበት በየአመቱ ሒሳብ መዝግያ ወቅት ይወስናል፡፡

**11 ከኩባንያው የሚጠበቁ ኣጠቃላይ ጥቅሞች**

11.1. በየአመቱ ለባለኣክስዮኖች የትርፍ ክፍያ ይደረጋል፣

11.2. የሃገሪቱ የኣውቶቡስ ትራንስፖርት ስርዓት በማሻሻል ህዝቡ የተሻሻለ ኣገልግሎት እንዲያገኝ ይረዳል፣

11.3. በተመጣጣኝ ዋጋ ለሕዝብ ትራንስፖርት እንዲዳረስ ያግዛል

11.4. የተሻሻለ የንግድና የንግድ ዕቃዎች እንቅስቃሴ በመፍጠር ዋጋን ለማረጋጋት ኣስተዋፅኦ ያደርጋል

11.5. ገበሬው ለገበያዎች እንዲቀርብ፣ ስለገበያዎችም እንዲያውቅ በመርዳት፣ ለሚገዛቸውና ለሚሸጣቸው ምርቶች አግባብ ያለው ዋጋ እንዲከፍል ወይም እንዲቀበል ይረዳል::

## 12. የመተዳደርያ ደንብ ጭማቂ

12.1 እያንዳንዱ ባለ አክስዮን በመደበኛና በአስቸኳይ ጉባኤዎች ድምፅ የመስጠት መብት አለው

12.2 የአክስዮን ልውውጥ ገደብ የለውም፡፡ ማንኛውም በህግ እውቅና ያለው ሰው ወይም አካል የአክስዮን ባለቤት መሆን ይችላል፡፡ አክስዮኖች በግልፅ ለገበያ ሊቀርቡና፣ ለውጭ ዜጎች ሊተላለፉ ይችላሉ፡፡

12.3 አክስዮኖች የሚመዘገቡት በአክስዮኑ ባለቤት ስም ብቻ ይሆናል፡፡

12.4 በአንድነት አክስዮን የገዙ ባለ አክስዮኖች ወኪል ይሰይማሉ፡፡ በወኪሉ ስምና አድራሻ ይመዘገባሉ፡፡ ኩባንያው ደግሞ ለወኪሉ ብቻ ያስታውቃል፡፡

## <u>13 ውክልናና የንብረት ግምት ማረጋገጥ</u>

ሰላም የህዝብ ማመላለሻ አ/ማ ጠቅላላ ንብረቱ አፍሪካ ንግድ ስራና ልማት አማካሪዎች /ኤቢዲ ኮንሰልት/ የተባለ አማካሪ ድርጅት እንዲገምት ውክልና ሰጥቶታል።

አፍሪካ ንግድ ስራና ልማት አማካሪዎች /ኤቢዲ ኮንሰልት/ የተባለ አማካሪ ድርጅት በ20/06/06 እ.ኤ.አ በወሰደው የንብረት ግምት መሰረት ኣጠቃላይ ንብረት ዋጋ ባንክ ያለው ገንዘብ ሳይጨምር ትክክለኛ ግምት ብር 32,077,555.00 እንደሆነ ያረጋግጣል።

## <u>14. ማ ስ ረ ጃ  ስ ለ መ ስ ጠ ት</u>

ከዚህ በታች የተዘረዘሩ የሰላም የህዝብ ማመላለሻ አክስዮን ማህበርን ሕጋዊነት የሚያረጋግጡ ሰነዶች መመርመር ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው በዋናው መ/ቤት በስራ ሰዓት ውስጥ ክፍት ሆኖ ይጠብቃሉ።

- የመመስረቻና የመተዳደሪያ ደንቦች
- የድርጅቱ ባለኣክስዮኖች የካፒታሉ 60% (ስልሳ በመቶ) በኣክስዮን መልክ ለሕዝብ እንዲሸጥ የተወሰነበት ቃለ ጉባኤ
- የንግድ ምዝገባ ሰርቲፊኬት
- የንግድ ፈቃድ
- የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት
- የውጭ አማካሪ ኮንሳልታንት የንብረት ግምት ሪፖርት

# ማጠቃለያ

6,000 አክስዮኖች የያንዳንዱ ዋጋ ብር 5000.00 (አምስት ሺህ ብር) በመላ ሃገሪቱ የሚገኙ የወጋገን ባንክ ቅርንጫፎች አማካይነት ለሽያጭ መቅረባቸውን ስናስታውቅ በደስታ ነው:: ምዝገባው ከጥቅምት 02 2006 ተጀምሮ ታህሳስ 31 2006 እ.አ.አ. ያበቃል::

እንደ አማካሪው ድርጅት ገለፃ የአውቶቡሶች፣ የጋራዥና በጋራዥ ውስጥ የሚገኝ ቋሚ ንብረት፣ የቢሮ ዕቃዎችና ቁሰቁሶች እንዲሁም በቅርብ ጊዜ የተገዙት ስቴሽን ዋገን ፎርድ ኤቨረስት እና የኒሳን ፓትሮል ባለ አንድ ጋቢና ተሽከርካሪዎች ዋጋ ግምት ተወስዷል::

የሚከተለው የዋጋ ግምት ውጤት ነው::

## የንብረት ዋጋ

| | | |
|---|---|---|
| ሀ/ አውቶቡሶች ከነሰርቪስ መኪኖች | ብር | 24,916,494.00 |
| ለ/ የጋራዥ ዕቃዎች | ብር | 286,060.00 |
| ሐ/ የቢሮ ዕቃዎች | ብር | 221,800.00 |
| መ/ ሕንፃዎች | ብር | 3,442,655.00 |
| ሠ/ ስቶክ | ብር | 1,666,971.00 |
| ረ/ መልካም ስም/ጉድ ዊል/ | ብር | 1,378,575.00 |
| ሸ/ ሌሎች መሳርያዎች | ብር | 165,000.00 |
| | | 32,077,555.00 |

አክስዮን ለመግዛት የሚፈልጉ ሁሉ በወጋገን ባንክ ቅርንጫፎች በመቅረብ የማመልከቻ ቅፆችን መሙላት ይገባቸዋል:: ክፍያው ለተገዛው አክስዮን በሙሉ የሚፈፀም ሲሆን ለእያንዳንዱ አክስዮን 50 ብር ለካፒታል መያዥ ወጪ ይጨምራል፡፡ ለአክስዮን ግዢ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ሁሉ የተሟለ አድራሻ እንዲኖራቸው ይገባል:: ስለዘህ የፓስታ ሳጥን ቁጥር ወይም ቋሚ የሆነ የተጠሪ አድራሻ መጥቀስ አስፈላጊ ነው:: በአክስዮን ግዢ መመዝገቢያ የተወሰነው ጊዜ ካበቃ በኋላ ለአመልካቾች በየአድራሻቸው የድልድል ደብደቤዎችን (ሌተር ኦፍ አሎትመንት) ይልካል:: ከዚህ በኋላ የተጠቀሱትን የድልድል ደብደቤዎችን እያቀረቡ ዋናውን የአክስዮን ምስክር ወረቀት መቀበል ይቻላል:: ይህ እስኪፈረም ድረስ ግን አክስዮኖቹ በገዢው ስም ተመዝግበው ይቆያሉ::